# የቦንድ ከጥቃት ጥበቃ

# ከጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

*ይህ ትርጉም በSocial Development Direct እና በTranslators Without Borders ለማሳወቅ ብቻ ታስቦ የተሰራ ነው። ትክክለኛነቱን BOND ማረጋገጥ አይችልም። ብቸኛው ኦፊሴላዊ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሲሆን የBOND* Safeguarding policy templates | Bond [ *ድረገጽ ላይ ይገኛል]፤*

## ዓላማ

የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ሰዎች በተለይ ደግሞ ሕፃናት፣ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎች እና የድጋፍ ተጠቃሚዎች ከ(መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት- 'መያድ') ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ጉዳት መጠበቅ ነው። ይህም በሚከተሉት ምክንያቶች የሚደርሱ ጉዳቶችን ያካትታል፤

- የ(መያድ) ሰራተኞች ወይም ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ስነምግባር
- የ(መያድ) ፕሮግራሞችና ተግባራት አቀራረፅ እና አፈፃፀም፡፡

ይህ ፖሊሲ (መያድ)ን ቁርጠኛ ውሳኔዎችን ይዘረዝራል፤ እንዲሁም ሰራተኞች እና ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች[1] ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ኃላፊነቶች በተመለከተ መረጃ ይሰጣል፡፡

ይህ ፖሊሲ የማይሸፍናቸው፤

- በስራ ቦታ የሚፈጸም ውሲባዊ ትንኮሳ፣ ይህ በ(መያድ) የፀረ ማንጓጠጥ እና ትንኮሳ ፖሊሲ ይታያል፡፡[2]
- በ(መያድ) ወይም በተጓዳኝ ተቀጣሪዎቹ የተፈፀሙ ሳይሆኑ ነገር ግን በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ስጋቶች፤

## ከጥቃት ጥበቃ ምንድን ነው?

በዩናትድ ኪግደም ውስጥ ከጥቃት ጥበቃ ማለት የሰዎችን ጤና፣ አጠቃላይ ደህንነትና ሰብዓዊ መብቶችን መጠበቅ እና ሰዎች ከጉዳት፤ ከጥቃትና ቸል ከመባል ነፃ ሆነው እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡[3]

በእኛ ዘርፍ ውስጥ ደግሞ ከጥቃት ጥበቃን የምንረዳው ሰዎች (ሕፃናትንና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎችን ጨምሮ) ከሰራተኞች ወይም ከፕሮግራሞች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ከሚመጩ ጉዳቶች መጠበቅ እንደሆነ አድርገን ነው፡፡

ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ትርጓሜዎች ከዚህ በታች ባለው አጭር መዝገበ ቃላት ውስጥ ተካትተዋል።

---

[1] ስለተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ትርጉም "ወሰን"ን ይመልከቱ

[2] በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸውና ከፕሮግራሞቻቸው ጋር ባሉ ግንኙነቶች ምክንያት የሚከሰቱ የስራ ቦታ ማንጓጠጥንና ትንኮሳን ከጥቃት ጥበቃ ፖርትፎሊያቸው ውስጥ እያካተቱ ይገኛሉ። ሆኖም በስራ ቦታ ለሚከሰቱ ማንጓጠጦችና ትንኮሳዎች በህግና በመንግስት በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሠረት የተቀመጡ ምላሾች የተለዩ ሊሆኑ በመቻላቸው ምክንያት በስራ ቦታ ላይ ለሚከሰት ማንጓጠጥና ትንኮሳ ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎች አብዛኛውን ጊዜ የተለዩ ሊሆኑ ይገባል፡፡

[3] ኤን.ኤች.ኤስ "ከጥቃት ጥበቃ ምንድነው?' ቀላል ንባብ እ.ኤ.አ 2011

# ወሰን

- በ(መያድ) ውስጥ በውል የተቀጠሩ ስራተኞች በሙሉ
- ከ(መያድ) ጋር በስራ ወይም በጉብኝት ምክንያት ግንኙነት ያላቸው ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች፤ እነዚህም አማካሪዎችን፤ በጎ ፈቃደኞችን፤ ሥራ ተቋራጮችን፤ የፕሮግራም ጎብኝዎችን (ጋዜጠኞችን ፣ ታዋቂ ሰዎችን እና ፖለቲከኞችን ጨምሮ) እና ከላይ የተጠቀሱትን ሳይወሰን ያካትታሉ፡፡

# የፖሊሲ መግለጫ

(መያድ) ማንኛውም ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በእድሜ፣ በፆታ ማንነት ፣ በአካል ጉዳት ፣ በፆታዊ ዝንባሌ ወይም በጎሳ መገለጫ ሳይለይ ከማንኛውም ዓይነት ጉዳት፣ ጥቃት፣ ቸል መባል እና ብዝበዛ የመጠበቅ መብት አለው ብሎ ያምናል። (መያድ) በሰራተኞች ወይም በተጓዳኝ ተቀጣሪዎች የሚፈፀሙ ጥቃቶችን እና ብዝበዛዎችን አይታገስም።

ይህ ፖሊሲ (እንደአግባብነቱ) የሚከተሉትን የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ይዳስሳል፤ የሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ፣ የአዋቂዎች ከጥቃት ጥበቃ እና ከወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት መጠበቅ፡፡ እነዚህ ቁልፍ ከጥቃት ጥበቃ ዘርፎች ከእነርሱ ጋር የተጎዳኙ የተለያዩ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች ሊኖራቸው ይችላል (ተጓዳኝ ፖሊሲዎችን ይመልከቱ)።

(መያድ) ከጥቃት ጥበቃ ስራውን የሚሰራው ሦስት ምሰሶዎችን መሠረት በማድረግ ሲሆን፤ እነርሱም- መከላከል፣ ሪፖርት ማድረግ እና ምላሽ መስጠት ናቸው፡፡

# መከላከል

## የ(መያድ) ኃላፊነቶች

(መያድ) የሚያደረጋቸው :

- ፖሊሲው ለሁሉም ሰራተኞች የደረሳቸው መሆኑን፤ ስለፖሲው ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን እና በፖሊሲው ውስጥ ያሉባቸውን ኃላፊነቶች ያወቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
- ፕሮግራሞች እና አተገባበራቸው ከ(መያድ) ጋር ግንኙነት በሚኖራቸው ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ከሚችል ማንኛውም ዓይነት አደጋ መከላከል በሚያስችል መልኩ መቅረፅ እና መተግበር። ይህ በፕሮግራሞቻችን ውስጥ ስለግልሰቦች መረጃ የምንሰበስብበትንና የምናሰራጭበትን መንገድ ያጠቃልላል፡፡
- በሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር እንዲሁም በሰራተኞችና በተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ስምሪት ላይ ጠንካራ ከጥቃት ጥበቃ ሥርዓቶችን መተግበር፡፡
- ሰራተኞች ለስራ ኃላፊነታቸው በሚመጥን ደረጃ ስለ ከጥቃት ጥበቃ ሥልጠና ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን በፍጥነት እና በህጉ መሠረት መከታተል፡፡

## የሰራተኞች ሃላፊነት

**የሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ**

የ(መያድ) ሰራተኞች እና ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ማድረግ የሌለባቸው፤

- እድሜው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ማንኛውም ሰው ጋር ውሲባዊ ድርጊቶችን መፈፀም፤

- በሕፃናት ላይ የወሲብ ጥቃት ወይም ብዝበዛ መፈፀም፤
- ሕፃናትን ለአካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም ስነልቦናዊ ጥቃት ወይም ለቸልታ መዳረግ፤
- የጉልበት ብዝበዛ ወይም ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ጨምሮ ሕፃናትን ለብዝበዛ በሚያጋልጡ ማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ

**የአዋቂዎች ከጥቃት ጥበቃ**

የ(መያድ) ሰራተኞች እና ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ማድረግ የሌለባቸው፤

- ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ላይ ወሲባዊ ጥቃት ወይም ብዝበዛ መፈፀም፤
- ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ለአካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም ስነልቦናዊ ጥቃት ወይም ለቸልታ መዳረግ፤

**ከፆታዊ ጥቃት እና ብዝበዛ መጠበቅ**

የ(መያድ) ሰራተኞች እና ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ማድረግ የሌለባቸው፤

- ለወሲብ ድርጊቶች በምላሹ ገንዘብን፣ የስራ ቅጥርን፣ ቁሶችን እና አገልግሎቶችን መቀበል ወይም መስጠት። ይህ በድጋፍ ተጠቃሚዎች ምክንያት የሚደረግን ማንኛውንም ዓይነት ልውውጥ ያካትታል፡፡
- ከድጋፍ ተጠቃሚዎች ጋር ማንኛውንም ዓይነት ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ፣ ምክንያቱም እነርሱ ተመጣጣኝ ባልሆነ የኃይል ሚዛን ሥር በመሆናቸው፤

የ(መያድ) ሰራተኞች እና ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች በተጨማሪነት የሚገደዱባቸው ጉዳዮች፡

- ከጥቃት ጥበቃ ጥሰቶችን የሚከላከል አካባቢን ለመፍጥርና ይህ ሁኔታም እንዲቀጥል ለማድረግ አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲሁም ከጥቃት ጥበቃ ፖሊሲው እንዲተገበር ማበረታታት፤
- ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ በ(መያድ) ሰራተኞች ወይም ተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ተፈፅመዋል ተብለው የሚታሠቡ ወይም የሚጠረጠሩ ጥሰቶችን አግባብነት ላለው ሰራተኛ ሪፖርት ማድረግ፤

# ለሪፖርቶች አበረታች ሁኔታን መፍጠር

(መያድ) ሰራተኞቻችን እና አብረናቸው የምንሰራቸው ማህበረሰቦች ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ሪፖርት ማድረግ የሚያስችላቸው ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ተገቢነት ያላቸው እና ተደራሽ የሆኑ የሪፖርት ማቅረቢያ መንገዶች መኖራችውን ያረጋግጣል።

ማንኛውም ሰራተኛ ስጋትን ወይም ቅሬታን መደበኛውን የጥቆማ ማቅረቢያ ሥርዓት ተከትሎ ሪፖርት ሲያቀርብ (ወይም ሲጠይቅ) በ(መያድ) የስራ ቦታ ብልሹ አሰራር የማጋለጥ (የመጠቆም) ፖሊሲ መሠረት ጥበቃ ይደረግለታል።

በተጨማሪም (መያድ) ከድርጅቱ ውጪ የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ይቀበላል (ለምሳሌ ከህብረተሰብ አባላት፣ ከአጋሮች እና ከመንግስት አካላት)።

### ከጥቃት ጥበቃ ስጋት እንዴት ሪፖርት ይደረጋል?

ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ስጋት ወይም ቅሬታ ያላቸው ሰራተኞች ስጋታቸውን ወይም ቅሬታቸውን (እንደአግባብነቱ) ለድርጅቱ ከጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ወይም ለቅርብ ሀላፊ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሆኖም ሰራተኞቹ ለከጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ወይም ለሃላፊ ሪፖርት ለማደረግ ምቾት ሳይሰማቸው ሲቀር ( ለምሳሌ ሪፖርቱ ትኩረት የማያገኝ መስሎ ሲሰማቸው ወይም ሪፖርት የሚደረግለት ሰው ከስጋቱ ጋር የተነካካ መስሎ

ሲሰማቸው) ስጋታቸውን ወይም ቅሬታቸውን ለማንኛውም ተገቢ ለሆነ የስራ ባልደረባ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ለምሳሌ ለከፍተኛ የስራ ሃላፊ ወይም ለሰው ሀብት አስተዳደር አካላት ሊሆን ይችላል።

(ዝርዝር የማግኛ አድራሻን ያስቀምጡ)

# ምላሽ መስጠት

(መያድ) ከጥቃት ጥበቃ ሪፖርቶችን ወይም ስጋቶችን በፖሊሲ እና ፖሊሲውን ለማስፈፀም በተዘረጉ ሥርዓቶች እንዲሁም በህግና በመንግስት በተደነገጉ ግዴታዎች መሠረት ክትትል ያደርጋል (ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ስላሉ ስጋቶች የሪፖርት እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓቶችን በተመለከተ በተጓዳኝ ፖሊሲዎች ውስጥ ይመልከቱ)።

(መያድ) ፖሊሲውን ተላልፈው በሚገኙ ስራተኞች ላይ ተገቢውን የስነምግባር/ዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፡፡

(መያድ) መደበኛ የሆውን የውስጥ ምላሽ ስራ (ለምሳሌ - ውስጣዊ የምርመራ ስራ) ካከናወነ በኋላም ይሁን ከማከናወኑ በፊት በሰራተኞቹ ወይም በተጓዳኝ ተቀጣሪዎቹ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ከጉዳቱ የተረፉ ሰዎች ድጋፍ ያቀርባል፡፡ ድጋፍን በተመለከተ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚመሩት ከጉዳት በተረፈው ሰው ይሆናል፡፡

# ሚስጥራዊነት

ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ በሚነሱ ስጋቶች ዙሪያ በሚሰሩ የሥራ ሂደቶች ውስጥ ሁሉ ሚስጥራዊነትን የመጠበቅ አስፈላጊት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ከስጋት እና ከጉዳዮች ክትትል ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ለሌላ ሰው/አካል ሊሰጡ የሚገባው መረጃውን መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆን አለበት፡፡ መረጃዎቹም በማንኛውም ጊዜ ደህንነታቸው በተጠበቀ አኳኋን መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

### ተጓዳኝ ፖሊሲዎች

የስነምግባር ደንብ

የፀረ ማንጓጠጥና ትንኮሳ ፖሊሲ

በሥራ ቦታ ብልሹ አሰራርን የማጋለጥ ( የመጠቆም) ፖሊሲ

የሕፃናት ከጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

የአዋቂዎች ከጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

በሰራተኞች ከሚፈፀሙ ፆታዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

የቅሬታዎች ፖሊሲ

ከጥቃት ጥበቃ ስጋት ሪፖርት የማድረግ እና ምላሽ የመስጠት ሥርዓት

በሰራተኞች ቅጥር ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ሥርዓት

እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ፖሊሲዎች

# አጭር መዝገበ ቃላት

**የድጋፍ ተጠቃሚዎች**

ከ(መያድ) ፕሮግራም ቁሶችን ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ የሚቀበል ማንኛውም ሰው፡፡ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም (መያድ) በሚያገለግለው ማህበረሰብ ውስጥም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፤ ይህም ባለስልጣን መሆንን በማሳየት ብዝበዛ መፈፀምን ሊያካትት የሚችል መሆኑን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

**ሕፃን**

ማንኛውም እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው፡፡

**ጉዳት**

የአካል፣ የአእምሮና እና ሌላ ማንኛውም ዓይነት የግለሰብ የሙብት ጥሰት

**የስነልቦና ጉዳት**

የስሜት ወይም የስነልቦና ጥቃት ሲሆን ይህም (በሚከተሉት ሳይወሰን) በሚያዋርድና ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ ማስተናገድን ለምሳሌ መልካም ባልሆነ የቅፅል ስም መጥራት፣ ያለማቋረጥ መተቸት፣ ማቃለል፣ ያለማቋረጥ ማሳፈር፣ ለብቻ በአንድ ቦታ ወስኖ ማስቀመጥ እና ከሌሎች መነጠልን ያካትታል፡፡

**ከፆታዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መጠበቅ**

ቃሉ በሰብአዊ እና በልማት ማህበረሰቡ ውስጥ ጥቅም ላይ እየዋለ ባለበት አግባብ መሠረት ድጋፍ የሚደረግላቸው ህብረተሰቦች በሰራተኞች ወይም በተጓዳኝ ተቀጣሪዎች ሊደርስባች ከሚችል ፆታዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል እንደሆነ ተደርጎ ይተረጎማል፡፡ ቃሉ የተወሰደው ከተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ ከወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ከሚያትተው መፅሔት ውስጥ ነው (ST/ SGB/2003/13)

**ከጥቃት ጥበቃ**

በዩናትድ ኪግደም ውስጥ ከጥቃት ጥበቃ ማለት የሰዎችን ጤና፣ አጠቃላይ ደህንነትና ሰብዓዊ መብቶችን መጠበቅ እና ሰዎች ከጉዳት፤ ከጥቃትና ቸል ከመባል ነፃ ሆነው እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡[4]

በእኛ ዘርፍ ውስጥ ደግም ከጥቃት ጥበቃን የምንረዳው ሰዎች (ሕፃናትንና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎችን ጨምሮ) ከሰራተኞች ወይም ከፕሮግራሞች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ከሚመነጩ ጉዳቶች መጠበቅ እንደሆነ አድርገን ነው፡፡ በአንድ ሊጋሽ የተሰጠ ትርጉም የሚከተለው ነው፡

ከጥቃት ጥበቃ ማለት ጉዳትን ለመከላከል (በተለይም ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ እንዳይከሰት)፤ ሰዎችን (በተለይም ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎችንና ሕፃናትን) ከጉዳቱ ለመጠበቅ እና ጉዳት ሲደርስም በአግባቡ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውንም ዓይነት አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ ማለት ነው፡፡

ይህ ትርጓሜ ከእሴቶቻችን እና ከመርሆዎቻችን የሚመነጭ ሲሆን ባህላችንንም ይቀርፃል። በተለይ ከወሲብ ዓላማ ጋር በተያያዘ ሊከሰት ከሚችል፣ ከተከሰተ ወይም ሙከራ ከተደረገበት ማንኛውም ዓይነት ስልጣንን፣ እምነትን፣ ተጋላጭነትን ያላአግባብ በመጠቀም ሊመጣ የሚችልን ጉዳት መከላከልና ምላሽ መስጠት ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡

ከጥቃት ጥበቃ ያለምንም ልዩ ሁኔታ በፕሮግራምቻችን፣ በአጋሮቻችን እና በሰራተኞቻችን ላይ ሁሉ ተግባራዊ ይደረጋል። ይህም ጉዳት የሚያስከትሉ አደጋዎችን፤ ብዝበዛዎችን እና ጥቃቶችን በንቃት መለየትን፤ መከላከልንና መጠበቅን እንዲሁም ችግር ሲከሰት ሪፖርት ለማድረግ፤ ምላሽ ለመስጠት እና በየጊዜው ለመማር የሚያስቸል ጠንካር፤ ተጠያቂነት ያለበትና ግልፅ ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል፡፡ የሚዘረጉት ሥርዓቶችም ተጎጂዎችን ማዕከል ያደረጉ እና ጥቃቱን መፈፀማቸው እስከሚረጋገጥ ድረስም ለተጠርጣሪዎች ተገቢውን ጥበቃ የሚሰጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከጥቃት ጥበቃ ተጠቃሚዎችን እና ከጉዳት የተረፉ ሰዎችን ማዕከል አድርጎ ይሰራል፡፡

**ወሲባዊ ጥቃት**

"ወሲባዊ ጥቃት" የሚለው ቃል በሀይል ወይም ተመጣጣኝነት በሌለው ወይም አስገዳጅ በሆነ መንገድ በድርጊት ወይም በማስፈራራት ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለውን የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ነው ፡፡

**ወሲባዊ ብዝበዛ**

"ወሲባዊ ብዝበዛ" የሚለው ቃል ማንኛውንም ተጋላጭነት ላይ ያለን አቅምና የሀይል አለመጣጣምን ወይም የተሰጠ እምነትን ያለአግባብ በመጠቀም ወይም ለመጠቀም በመሞከር ለወሲብ አላማ አድርጎ መጠቀም ሲሆን፤ ይህም በሚከተሉት ሳይወሰን ሌላውን በወሲብ ከመበዝበዝ የሚገኝን የገንዘብ፤ የማህበራዊና የፖለቲካ ትርፍን ያካትታል፡፡ ይህ ትርጉም የሰዎች ግህገወጥ ዝውውርን እና ዘመናዊ ባርነትን ይጨምራል።

**ከጉዳት የተረፈ**

ጥቃት ወይም ብዝበዛ የተፈጸመበት ሰው። "ከጉዳት የተረፈ" የሚለው ቃል ጥንካሬን፤ መቋቋምን እና ለመኖር መቀጠል ያለውን አቅም የሚያመለክት ስለሆነ ብዙውን ጊዜ "ተጠቂ" በሚለው ቃል ምትክ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ሆኖም ግለሰቦች ራሳቸውን እንዴት መግለፅ እንደሚፈልጉ የግል ምርጫቸው ይሆናል፡፡

**አዋቂ ለአደጋ ተጋላጭ**

አንዳንድ ጊዜ ተጋላጭ አዋቂ ተብሎም ይጠራል፡፡ በአእምሮ ወይም በሌላ የአካል ጉዳት ፣ በእድሜ ወይም በህመም ምክንያት እንክብካቤ እየተደረገለት ያለ ወይም የሚፈልግ እና እራሱን/ሷን መንከባከብ ወይም ከጎላ ጉዳት ወይም ብዝበዛ መጠበቅ የማይችል/የማትችል ወይም ምናልባት ሊያቅተው የሚችል ሰው፡፡

---

[4] ኤን.ኤች.ኤስ "ከጥቃት ጥበቃ ምንድነው?' ቀላል ንባብ እ.ኤ.አ 2011